# የጥገኝነት ሂደት አጠቃላይ ዳሰሳ

***ጥገኝነት ፍለጋ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የሚመጡት ሰዎች ሁሉ በዘር፣ በኃይማኖት፣ በዜግነት፣ በተወሰነ የማኀበራዊ ቡድን አባልነት፣ ወይም በፖለቲካ አቋም ምክንያት መሳደድ ስለደ ረሰባቸው ወይም ሊደርስባቸው የሚችለውን መሣደድ በመፍራት ነው። ለጥገኝነት ብቁ ሆነው የተገኙት አመልካቾች በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ለመቆየት ሊፈቀድላቸው ይችላል።***

**ለጥገኝነት ምንድነው?**
ጥገኝነት አንድ ብቁ ስደተኛ ተሰዶ ወደመጣበት አገር ከመባረር ስጋት ነፃ ሆኖ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ መቆየት፣ በሂደትም ሕጋዊ ቋሚ የነዋሪነት ፈቃድ ማግኘት የሚችልበት የከለላ ቅርፅ ነው።

**ለጥገኝነት ማመልከት የሚችለው ማን ነው?**
በወቅቱ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሚገኝ ወይም ወደዚህ አገር (በኤርፖርት፣ በባህር በር ወይም ድምበር በማቋረጥ) መግቢያ ቦታ የሚፈልግ የማንኛውም አገር ዜግነት ያለው ማንኛውም ግለሰብ ነው።

**ለጥገኝነት ማመልከት ያለብኝ መቼ ነው?**
በአጠቃላይ ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ከገባህበት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የጥገኝነት ማመልከቻ ማቅረብ አለብህ። ይህ ደምብ ከማይመለከታቸው መካከል 1) ለጥገኝነት ብቁ የሚያደርግህን መሠረታዊ መመዘኛ ሁኔታ የሚቀይር በአገርህ የከሰተ ለውጥ መሠረታዊ መመዘኛ ሁኔታ የሚቀይር በአገርህ የተከሰተ ለውጥ 2) የጊዜ ገደቡ ካለፈ በኋላ ማመልከቻህን ካስገባህበት ሁኔታ የተያያዘ ልዩ ምክንያት ካለ እነዚህን ሁኔታዎች ሊያካትት ይችላል።

**በህገ ወጥ መንገድ እዚህ የምኖር ከሆንኩ ለጥገኝነት ማመልከት እችላለሁ?**
አዎን። የስደተኝነት ይዞታህ ምንም ይሁን ምን ለመጨረሻ ጊዜ እዚህ አገር በገባህበት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የጥገኝነት ማመልከቻህን እስካስገባህ ድረስ ወይም ይህ ደምብ ለማይመለከታቸው መመዘኛ ብቁ የሚያደርግህን ሁኔታ የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ከቻልክ ማመልከት ትችላለህ።

**በወንጀል ክስ በፍርድ ቤት ቅጣት ተበይኖብኝ የማውቅ ከሆነ ማመልከት እችላለሁ?**
አዎን። ሆኖም እንደ ወንጀሉ ጠባይ ጥገኝነት ልትከለከል ትችላለህ።

**ማመልከቻ ከማስገባት ወይም ጥገኝነት ከማግኘት ልከለከል እችላለሁ?**
ከዚህ ቀደም የጥገኝነት ማመልከቻ አቅርበህ ወይም በኢሚግሬሽን ዳኛ ወይም በኢሚግሬሽን ይግባኝ ሰሚ ቦርድ ውሳኔ ተከልክለህ የምታውቅ ከሆነ፣ ለመጨረሻ ጊዜ ወደዚህ አገር በገባህበት በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ማመልከቻህን ካስቀረብህ ወይም በሁለትዮሽ ወይም በብዙ ወገን ስምምነት መሠረት የደህንነት ከለላ ወደምታገኝበት ሦስተኛ አገር ልትዛወር ከቻልክ የጥገኝነት ማመልከቻ እንዳታቀርብ ልትከለከል ትችላለህ። በአንዳንድ የወንጀል ድርጊቶች ምክንያት፣ ከደህንነት በተያያዙ ጉዳዮች ምክንያት ወይም ሌሎች ሰዎችን በማሣደድ ድርጊት ተሣትፎ ከነበረህ ወይም ቀደም ሲል በሌላ አገር ኑሮህን መስርተህ ውጪ አገር የምትኖር ከሆንክ የጥገኝነት ሕጋዊ ፈቃድ ላይሰጥህ ይችላል። ይህ አጠቃላይ ደምብ የማይመለከታቸው ጉዳዮች መኖራቸው አይቀርም። የጥገኝነት ማመልከቻ ከማቅረብ ከተከለከልክ ግን አንድም ከአገር የመባረር ውጤት ተፈፃሚ እንዳይሆን ቀሪ ሊደረግልህ አሊያም በመባረር ሥነ ሥርዓት በይበልጥ ገደብ ያለበት የከለላ ቅርፅ እንድታገኝ ሊደረግ ይችላል።

# የጥገኝነት አሠራርን በተመለከተ ብዙውን ጊዜ የሚነሱ ጥያቄዎች

**ለጥገኝነት ማመልከት የምችለው እንዴት ነው?**
ለጥገኝነት ማመልከቻ ለማቅረብ የጥገኝነትና የመባረር ማስቀሪያ ማመልከቻ ቅጽ አይ-159 መሙላት አለብህ፤ መመሪያውን በጥንቃቄ መከተል ይኖርብሃል። የማመልከቻ ቅፅ በቀጥታ መስመር በኢንተርኔት አድራሻ http://www.usics.gov/forms ላይ ማግኘት ወይም በቅፅ ጥያቄ ማስተናገጃ ስልክ ቁጥር 1-800-870-3676 በመደወል መጠየቅ ይቻላል።

**ለጥገኝነት ማመልከቻ የሚጠየቀው የአገልግሎት ክፍያ ምን ያህል ነው?**
ለጥገኝነት ማመልከቻ የሚጠየቅ ምንም አይነት የአገልግሎት ክፍያ የለም።

**በማመልከቻዬ የባለቤቴንና የልጆቼንም ጉዳይ በአንድ ላይ ማቅረብ እችላለሁ?**
ማመልከቻ በምታቀርብበት ጊዜ ባለቤትህና ልጆችህ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሚገኙ ከሆነ ወይም በአቤቱታህ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥበት ድረስ በማንኛውም ጊዜ የነርሱንም ጉዳይ በማመልከቻ አካተህ ባንድ ላይ ማቅረብ ትችላለህ። ማንኛውም ልጅ በማመልከቻህ ውስጥ በጥገኝነት መካተት የሚችለው እድሜው ከ21 ዓመት በታች ከሆነ ነው። እነዚህን ጥገኞች ይዘህ ለጥገኝነት ቃለመጠይቅህ መቅረብ አለብህ።

**ለጥገኝነት ባመለክት የደህንነትና የህይወት ታሪክ ሪከርድ ማጣሪያ ይደረግብኛል?**
አዎን። ለጥገኝነት ማመልከቻ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው የደህንነትና የህይወት ታሪክ ሪከርድ ማጣሪያ ይደረግበታል። በዚሁ ማጣሪያ ውጤት መሠረት ጥገኝነት ለማግኘት ብቁ ሣትሆን ልትገኝ ትችላለህ።

**ለጥገኝነት ባመለክት የጣት አሻራ የመስጠት ቆይታ አለብኝ?**
አዎን። የጥገኝነት ማመልከቻ ቅፅህን ከሞላህ በኋላ በማመልከቻ ድጋፍ ማዕከል የጣት አሻራህ የሚወስድበትን ሰዓት፣ ቀን ቦታ የሚገልፅ ደብዳቤ ይደርስሃል።

**የጥገኝነት ማመልከቻ ካስገባሁ በኋላ ተቀጥሬ መስራት እችላለሁ?**
የጥገኝነት ማመልከቻ ስታቀርብ በዚሁ ጊዜ የሥራ ፈቃድ ማመልከቻ ማቅረብ አትችልም። ሆኖም የተሟላ የጥገኝነት ማመልከቻህን ካስገባህ በኋላ በማመልከቻህ ላይ ምንም ዓይነት ውሳኔ ሣይሰጥበት ባንተ ምክንያት የተፈጠረውን ማንኛውንም መጓተት ሣይጨምር 150 ቀናት ካለፉ የሥራ ፈቀድ ማመልከቻ ማስገባት ትችላለህ። በተጨማሪም ጥገኝነት ከተሰጠህ፣ የጥገኝነት አቤቱታህ እንደፀደቀ ወዲያውኑ የሥራ ፈቃድ ይሰጥሃል።

**የጥገኝነት ማመልከቻ ካስገባሁ በኋላ ከዩናይትድ ስቴትስ ውጪ ጉዞ ማድረግ እችላለሁ?**
በጥገኝነት ማመልከቻህ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ከዩናይትድ ስቴትስ ውጪ ወደሌላ ማንኛውም አገር ጉዞ ማድረግ ካለብህ በቅድሚያ አድቫንስ ፓሮል በሚል መጠሪያ ጭምር የሚታወቀውን ተመልሶ መግቢያ ዋስትና ፈቃድ ዩናይትድ ስቴትስን ከመልቀቅህ በፊት ማግኘት አለብህ። በቅድሚያ ተመልሶ መግቢያ ዋስትና ፈቃድ ሣታመጣ ብትቀር በዩኤስሲአይኤስ በኩል ማመልከቻህን እንደተውከው ይቆጠራል፣ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ተመልሰህ እንዳትገባ ፈቃድ ልትከለከልም ትችላለህ። በተጨማሪም ተመልሶ መግቢያ ዋስትና ፈቃድ ወስደህ የመሰደድ ስጋት ወዳለበት አገር ከተመለስክ ለተመለስክበት አሣማኝ ምክንያት ማቅረብ ካልቻልክ በስተቀር ዩኤስሲአይኤስ የጥገኝነት ማመልከቻህን ትተኸዋል ብሎ ሊወስን ይችላል።

**ማን ነው በጥገኝነት ቃለመጠይቅ ጊዜ እኔን የሚረዳኝ?**
የራስዎን ጠበቃ ወይም የሕግ ተወከይ የዩኤስ መንግስትን ወጪ ሳያስወጡ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

**እንግሊዝኛ መናገር የማልችል ከሆነ ቃለ መጠይቅ የሚደረግልኝ እንዴት ነው?**
በአስተርጓሚ አማካኝነት ቃለ መጠይቅ ይደረግለታል። ዩኤስሲአይኤስ አስተርጓሚ አያቀርብም። ለቃለ መጠይቁ የራስህን አስተርጓሚ ይዘህ መምጣት አለብህ። አስተርጓሚህ እንግሊዝኛ የመናገር በቂ ችሎታ ከሌለው የተሻለ ችሎታ ያለው አስተርጓሚ ማግኘት እንድትችል ለሚደረግልህ ቃለ መጠይቅ ተለዋጭ ቀጠሮ ሊያዝልህ ይችላል።

**ለቃለ መጠይቅ በምቀርብበት ጊዜ የሚኖረው ሁኔታ ምን ይመስላል?**
በጥገኝነት ጉዳይ መስሪያ ቤቱ ተገኝተህ ከጥገኝነት መኮንን ጋር ጉዳት የሌለበት ቃለ መጠይቅ ታደርጋለህ። መኮንኑ ማንነትህን ያጣራል፣ መሠረታዊ የግል ህይወት ታሪክህንና ለጥገኝነት የምታመለክቱበትን ምክንያት የሚመለከቱ ጥያቄዎች ይጠይቅሃል። በቃለ መጠይቁ ሂደት የምትናገረው ሁሉ በሚስጥር ይያዛል። የሥራ ልምድህን በሚመለከት ማንኛውንም መረጃ በተቻለ መጠን በዝርዝር ለጥገኝነት መኮንኑ መናገር በጣም አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም እንደ ስደተኛ ብቃት ያለህ መሆኑ ወይም አለመሆኑ በጥገኝነት መኮንኑ ሊወሰን የሚችል በመሆኑ ነው። በጉዳይህ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የጥገኝነት ቃለመጠይቁ በተደረገበት ቀን የሚሰጥ አይደለም።

**ለጥገኝነት ብቁ መሆን አለመሆኔ በጥገኝነት መኮንኑ የሚወሰነው እንዴት ነው?**
የጥገኝነት ትርጓሜን የምታሟላ መሆን አለመሆንህን በሚመለከት በጥገኝነት መኮንኑ በሚደረግ ምዘና ለጥገኝነት ብቁ መሆን አለመሆን ይወሰናል፤ በማመልከቻህ ላይ የሞላኸውንና በቃለመጠይቁ ጊዜ በጥገኝነት መኮንኑ የሰጠኸውን መረጃ፣ እንዲሁም መኮንኑ ሊያገኝ የሚችለውን ሌላ መረጃ መነሻ በማድረግ ጥገኝነት የሚሰጥህ ወይም የማይሰጥህ መሆኑ ይወሰናል።

**ለጥገኝነት ብቁ የሚያደርገውን መመዘኛ ሳላሟላ ብገኝ የሚከተለው ምን ይሆናል?**
ተቀባይነት ያለው የስደተኝነት ይዞታ ለማግኘት ብቁ የሚያደርገውን መመዘኛ ሳታሟላ ብትገኝ ወይም በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ለመቅረት (በጊዜያዊ ከለላ ወይም በአንዳንድ ሁኔታዎች በዋስትና) መመዘኛውን ካሟላህ ለጥገኝነት ብቁ ሣትሆን የተገኘህበትን ምክንያት የሚገልፅ አቤቱታህ ውድቅ ማድረግ የተፈለገበትን ሃሣብ የሚጠቅስ ደብዳቤ ይደርስሃል። በእነዚህ ምክንያቶች ላይ መከራከሪያና አቤቱታህን የሚደግፍ ተጨማሪ ማስረጃ የማቅረብ እድል ይኖርሃል። ተቀባይነት ያለው የስደተኝነት ይዞታ ከሌለህ ወይም ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ለመቆየት የሚያስችለውን መመዘኛ ካላሟላህ ከአገር የማባረር እርምጃ የሚጠይቅ ክስ ይመሠረትብሃል፣ ጉዳይህም የጥገኝነት ጥያቄህን እንደ አዲስ ወደሚመለከት የኢሚግሬሽን ዳኛ ይመራል።

**ጉዳዩ የደረሰበትን ደረጃ እንዴት ማወቅ እችላለሁ?**
የጥገኝነት ቃለ መጠይቅህን ያካሄደውን ወይም የሚያካሂደውን የዩኤስአይሲኤስ የጥገኝነት መስሪያ ቤት ማነጋገር ትችላለህ።

**ህጉን የት ማግኘት እችላለሁ?**
ጥገኝነትን የሚመለከተው የሕግ መሠረት ለጥገኝነት ብቁ የሚያደርጉትን መመዘኛዎች ከሚጠቅሰው የኢሚግሬሽንና ዜግነት የፌዴራል ደምብ ክፍል 208 የሚነሳ ሲሆን የጥገኝነት ሥነ ሥርዓቱን ደግሞ በፌዴራል ደምቡ (ሲኤፍአር) አንቀፅ 8 እና 208 ማግኘት ይቻላል።

U.S. Citizenship and Immigration Services

# የጥገኝነት የድጋፍ እርምጃ አጭር ዳሰሳ

**ደረጃ አንድ: ጥገኝነት ፈላጊ ዩናይትድ ስቴትስ ይገባል**

አንድ ጥገኝነት ፈላጊ 1) ዩናይትድ ስቴትስ ከገባ ወይም በአካል ከተገኘ እንዲሁም 2) ዩናይትድ ስቴትስ በገባ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ማመልከቻ ካስገባ ወይም አጠቃላይ ደምቡ የሚጠይቀውን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ማመልከቻ የማስገባት ግዴታ የማይመለከተው መሆኑን ማስረዳት ከቻለ በአጠቃላይ በአይኤንኤ አንቀፅ 208 (ሀ) መሠረት የጥገኝነት ማመልከቻ ማስገባት ይችላል፡፡

**ደረጃ ሁለት: ጥገኝነት ፈላጊ የጥገኝነት ማመልከቻ ያስገባል**

ጥገኝነት ፈላጊ የጥገኝነትና የመባረር የማስቀሪያ ማመልከቻ ቅፅ አይ-589 ሞልቶ ለሚመለከተው የአገልግሎት ማዕከል ያስገባል፡፡

**ደረጃ ሦስት: የአመልካች የጣት አሻራና የደህንነት የህይወት ታሪክ ሪከርድ ማጣሪያ ይካሄዳል**

እድሜያቸው 13 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናቸው አመልካቾች ወደማመልከቻ ድጋፍ ማዕከል ወይም ሥልጣን ወደተሰጠው ሕግ አስከባሪ መሥሪያ ቤት ሄደው የጣት አሻራ እንዲሰጡ የሚጠይቅ ደብዳቤ ይደርሳቸዋል፡፡

**ደረጃ አራት: አመልካች የቃለ መጠይቅ ማሣወቂያ ደብዳቤ ይደርሰዋል**

ብዙውን ጊዜ አመልካቾች የተሟላ የማመልከቻ ቅፅ አይ-589 ካቀረቡ በኋላ በ21 ቀን ጊዜ ውስጥ ብዙውን ጊዜ አመልካቾች ቃለ መጠይቅ የሚያደርጉበትን ቀን፣ ቦታና ሰዓት የሚጠቅስ ደብዳቤ ይደርሳቸዋል፡፡

**ደረጃ አምስት: አመልካች ቃለ መጠይቅ ያደርጋል**

አመልካቹ በአርሊንግተን (ቨርጂኒያ)፣ ቺካጎ (ኢሊኖይ)፣ ሂውስተን (ቴክሳስ)፣ ሎስ አንጀለስ (ካሊፎርኒያ)፣ ሚያሚ (ፍሎሪዳ)፣ ኒዎርክ/ሊንድሃርለት (ኒውጀርሲ)፣ ኒውዮርክ /ሮስዴል (ኒውዮርክ) እና ሣን ፍራንሲስኮ (ካሊፎርኒያ) ከሚገኙት ስምንት የጥገኝነት መሥሪያ ቤቶች በአንዱ ወይም አመልካቹ የጥገኝነት መሥሪያ ቤት ከሚገኝበት ርቆ የሚኖር ከሆነ በዲስትሪክት መሥሪያ ቤት ቃለ መጠይቅ ይደ ረግለታል፡፡

በአብዛኛው አመልካቾች ማመልከቻ ባስገቡ በ43 ቀን ጊዜ ውስጥ ምናልባትም የጥገኝነት መኮንኖች ወደነዚህ መሥሪያ ቤቶች ለመጓዝ ዝግጅት ማድረግ ስላለባቸው ከዚህ በሚበልጥ ጊዜ ውስጥ በዲስትሪክት መሥሪያ ቤት ለግለሰቦች በሚያዘው የቃለ መጠይቅ ቀጠሮ መሠረት ቃለ መጠይቅ ይደረግላቸዋል፡፡

**ደረጃ ስድስት: የጥገኝነት መኮንን መመዘኛውን የሚያሟሉ አመልካቾችን ይወስናል: ተ ቆጣጣሪ የጥገኝነት መኮንን ውሳኔውን ያጣራል**

የጥገኝነት መኮንኑ አመልካቹ በአይኤንኤ አንቀፅ 101 (ሀ) (42) (ሀ) መሠረት የጥገኝነት ትርጓሜውን የሚያሟላ መሆን አለመሆኑን ወይም በአይኤንኤ አንቀፅ 208 (ለ) (2) መሠረት ጥገኝነት የሚከላከል መሆን አለመሆኑን ይወስናል፡፡ ተቆጣጣሪ የጥገኝነት መኮንን የጥገኝነት መኮንኑ ውሳኔ ከሕጉ ድንጋጌ የሚጣጣም መሆን አለመሆኑን ያጣራል፡፡

**ደረጃ ሰባት: አመልካች ውሳኔ ይደርሰዋል**

በአብዛኛው አመልካቾች ቃለ መጠይቅ ካደረጉ ከሁለት ሣምንት በኋላ ውሳኔውን ለመውሰድ ወደ ጥገኝነት መሥሪያ ቤቱ ይመለሳሉ፡፡ አመልካቹ ማመልከቻ ካስገባ በጠቅላላው ከ60 ቀናት ጊዜ በኋላ ውሳኔው ይደርሰዋል፡፡

በአቤቱታዎች ላይ የሚሰጡ ውሳኔዎች በእንጥልጥል ላይ በሚገኙ የደህንነትና የግል የህይወት ታሪክ ሪከርድ ማጣሪያ ሥራዎች ምክንያት ሊዘገዩ ይችላሉ፡፡

በወቅቱ ተቀባይነት ያለው ይዞታ ላላቸው፣ በዲስትሪክት መሥሪያ ቤት ቃለ መጠይቅ ለተደረገላቸው ወይም ጉዳያቸው በጥገኝነት ዲቪዥን ዋና መሥሪያ ቤት ሠራተኞች በመታየት ላይ ለሚገኝ አመልካቾች የአሠራር ሂደቱ ረዘም ያለ ጊዜ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ በእነዚህ ሁኔታዎች ውሳኔው በአጠቃላይ በፖስታ ቤት ለአመልካቾች ይላካል፡፡

# ተጨማሪ አገልግሎት

ለጥገኝነት ቃለ መጠይቅ ለዩናይትድ ስቴትስ መንግስት የሚከፈል ምንም ዓይነት ክፍያ በሌለበት የራስህን የሕግ ወኪል ማቅረብ ትችላለህ፡፡ በሚከተሉት ጉዳዮች ሊረዱህ የሚችሉ ፕሮቦኖ (በነፃ ወይም በቅናሽ ዋጋ) አገልግሎት የሚሰጡ ጠበቆች ወይም በማኅበረሰብ ላይ የተመሠረቱ ለትርፍ ያልቆሙ ድርጅቶች ዝርዝር ማግኘት ትችላለህ፡፡ በዚህ አማካኝነት

- ነፃ የሕግ ምክር የሚሰጡ ሙያተኞችን ዝርዝር የያዘ ድረ ገጽ ማየት
- **የማመልከቻ ቅፅ ለማግኘት በስልክ ቁጥር 1-800-870-3676**
- በፍትህ ዲፓርትመንት የኢሚግሬሽን ሪቪው የድረ ገፅ አድራሻ http://www.usdoj.gov/eior ላይ አስፈላጊውን መረጃ ማግኘት
- በአቅራቢያህ የሚገኘውን የጥገኝነት መሥሪያ ቤት ወይም የዲስትሪክት መሥሪያ ቤት መጠየቅ ይቻላል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን (ዩኤንኤችሲአር) በቅፅ አይ-589 አሞላል ሊረዱህ የሚችሉ ሰዎችን ለመለየት ሊረዳህ ይችላል፡፡ ዩኤንኤችሲአርን ለማነጋገር በስልክ ቁጥር (202) 296-5191 መደወል ወይም በድ ረ ገፅ አድራሻው http://www.unher.org ዝርዝር መረጃ ማግኘት ይቻላል፡፡

***በዚህ በራሪ ወረቀት ላይ የተገለፁትን ርዕሶች በሚመለከት ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገ፡ በድረ ገፅ አድራሻ http://www.usics.gov/asy/um ማግኘት ወይም በስልክ ቁጥር 1-800-375-5283 በመደወል መጠየቅ ይቻላል፡፡***

U.S. Citizenship and Immigration Services

ከለላ • ታማኝነት • አገልግሎት

# የዩኤስሲአይኤስ የጥገኝነት ፕሮግራም

(USCIS ASYLUM PROGRAM)



## ለዕጩ የጥገኝነት አመልካቾች የተዘጋጀ መመሪያ

U.S. Citizenship and Immigration Services

www.uscis.gov/asylum